በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን።

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? …

# *ፕሮቴስታንት እና ክፍፍሎቹ*

# ክፍል ስድስት

**በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**በሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

መጋቢት ፲፯ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# 1. ካልቪኒዝም (Calvinism)

- ጆን ካልቪን ከ1509-1569 ዓ.ም. የኖረ ፈረንሳዊ ሰው ነበር፡፡
- በ24 ዓመቱ ካቶሊክን ትቶ ፕሮቴስታንት ሆነ፡፡ የፕሮቴስታንት ተከታዮችንም ለማደራጀት #ኢንስቲትዩትስ; (Institutes) የተሰኘ መጽሐፍ ጻፈ፡፡ ተከታዮቹም ካልቪኒስት ተባሉ፡፡ እርሱም ትምህርቱ እንደ ሉተር (መካነ ኢየሱስ) ነበር፡፡
- ካልቪኒዝም በስዊዘርላንድ፤ በኒው ኢንግላንድ፤ በምዕራብ አውሮፓ፤ በእንግሊዝ፤ እንዲሁም በአሜሪካ ደግሞ በፕሪስባይቴሪያኒዝም ስም ተቀባይነት አገኘ፡፡
- የሪፎርሜሽን እንቅስቃሴ የወለዳቸው የፕሮቴስታንት ዘርፎች ሪፎርማል ቸርችስ ተብለው የሚጠሩ ሲሆን ከነርሱም መካከል ካልቪኒዝምና ፕሪስባይቴሪያን ይገኛሉ፡፡
- ካልቪኒስቶች በአሜሪካና በአውሮፓ ሪፎርማል ቸርችስ ሲባሉ፤ በብሪታንያና በዩናይትድ ስቴትስ ፕሪስባይቴሪያን ተብለው ይጠራሉ፡፡ አስቀድሞም የደች ሪፎርምድ ቸርች ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡
- አንግሊካን ቸርች ደግሞ ከካቶሊክ ከሉተርና ከካልቪን ትምህርቶች በማቀላቀል እንደ ፕሮቴስታንትና፤ ካልቪኒዝም በንጉሥ ሄንሪ በ1536 ዓ.ም. በእንግሊዝ ፓርላሜንት የተፈጠረ ነው፡፡
- ካልቪን #ኢየሱስ አይሁድን ብቻ ሊያድን የመጣ ነው; በማለት <u>ሮሜ 9፡6-8</u> ን ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በመነጠል ያስተምራል፡፡ መጽሐፍ ግን #*<u>ሰዎች ሁሉ</u> ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው፡፡*; <u>1ኛ ጢሞ 2፡3-4</u>፤ #*ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን <u>ሁሉ</u> ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል፡፡!*; <u>2ኛ ጴጥ 3፡9፡፡</u> ይላል፡፡

## 3. ባፕቲስት (Baptist Church)

- እንቅስቃሴው በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተጀምሮ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ቁጥራቸው እየጨመረ መጣ። ቅርንጫፎቻቸውም ወደ ሃያ ይጠጋሉ። ሁሉም ቢለያዩም ሕፃናት መጠመቅ የለባቸውም በማለት ግን አንድ ናቸው። ማቴ 19፡14፣ ዮሐ 3፡5፣ ሉቃ 2፡22-24፣ የሐ. ሥራ 16፡15፣ ዘሌዋ 12፡1-8...ግን ይህን አያስተምሩምም።
- በ1600 ዓ.ም. የነበረው ጆን ስሚዝ ከፕሮቴስታንት ትምህርት በወጣ መልኩ እንደገና ሕፃናትን ማጥመቅ በመጀመሩ ከእንግሊዝ ተሰዶ በመጀመሪያ ወደ ሆላንድ በመቀጠልም የአሜሪካ ቅኝ ግዛት ወደ ሆኑ አገሮች ከእንግሊዛውያን ባለሥልጣናት ሸሽቶ በመሄድ ባፒቲስት ቸርችን አቋቁሞታል።
- ባፕቲስቶች የሃይማኖት መሪ የላቸውም። መጽሐፍ ቅዱስን በነጻነት አንብበን በገባን ትርጉም መመራት አለብን ባዮች ናቸው። ሮጀር ዊሊያምስ በ1635 ዓ.ም. በአሜሪካን አገር በምትገኝ ደሴት የባፒቲስቶችን ማኅበር መስርቷል።
- ባፕቲስቶች በመጨረሻ የጥቁር አሜሪካውያንን ልብ ከዶግማ፣ ከቀኖና፣... የጸዳን ነን... ለሽማግሌዎችና ወላጅ ለሌላቸው የመኖሪያ፣ የሕክምና፣ የትምህርት እርዳታ በፈቃደኛ አማኞቻችን እናደርጋለን... እያሉ ማርከው በእንግሊዝ፣ በጀርመን፣ በቻይና፣ በጃፓን፣ በሕንድ፣ በፖላንድ፣ በሩሲያ... ተስፋፍተዋል። ባፕቲስቶች የሥላሴን፣ ሲኦል፣ ዲያቢሎስ ትምህርት አይቀበሉም። እምነት ብቻ በቂ ነው ይላሉ። ያዕ. 2፡14-19 ግን የሥራንም አስፈላጊነት ያስረዳል።

## 4. ሜቶዲስት (Methodist Church)

- በ1784 ዓ.ም. ከእንግሊዝ ቸርች ተገንጥለው በአሜሪካ ሜቶዲስት ቸርች ተብለው ተቋቋሙ። መሥራቾቻቸውም ጆን ዊስሌይ፣ ቻርልስ ዊስሌይና ጆርጅ ዘዋይት የተባሉ ሰዎች ናቸው።
- ሥርዓትና ዘዴ (*Rule of Method*) የሚል መጽሐፍ ጽፈው ስለነበር በዚህ የተነሳ ተከታዮቻቸው ሜቶዲስቶች ተብለዋል። በውሳጣቸውም ብዙ ክፍፍሎች አሉ።

## 5. ሜኖናይት (Mennonites Church)

- በ1559 ዓ.ም. ሜና ሳይመንስ በተባለው የደች ተወላጅ የተቋቋመ ማኅበር ነው፡፡ብዙ ቅርንጫፎች አሉአቸው፡፡ እርስ በርሳቸው በብዙ ቢለያየየም የሕፃናትን ጥምቀት ባለማጥመቃቸው፤ ጥምቀትም ሆነ ሥጋውና ደሙ ምሳሌ እንጂ አማናዊ አይደሉም በማለታቸው ግን ይመሳሰላሉ፡፡ እንቅስቃሴአቸውም ሃይማኖትን እንደ ሽፋን በመጠቀም የተቋቋመ ማኅበራዊና ፓለቲካዊ አጀንዳ የነበረው በሃይል በመጠቀም በዝርፊያና በግድያም የተመሠረተ ነው፡፡

- ሚሽ የሚባሉት ሜኖናውያን በጦርነት አንዋጋም፤ አንምልም... በማለት ለየት ያለ ትምህርት አላቸው፡፡ እነዚህም በ1683 ዓ.ም. ጃኮብ ኦማን ማኅበራቸውን መስርቶ በፔንሲልቫንያ ግዛት መኖር ከጀመሩ በኋላ በርሱ ስም አሚሽ ተባሉ፡፡
- እነዚህ በጠንካራ ሠራተኛነታቸው፤ ጥብቅ በሆነ ምግባራቸውና ታማኝነታቸው እንደ ሆላንድ፤ ሩሲያ፤ እንግሊዝና ሰሜን አሜሪካ ባሉ አገሮች ያታወቃሉ፡፡

## 6. ጴንጤዎች (Pentecostalism)

- በአሜሪካ ቶፔካ በተባለው የካንሰስ ግዛት በ1901 ዓ.ም. ቻርለስ ፓርሃም በተባለው ሜቶዲስት የተመሰረተ መጤ እምነት ነው፡፡
- ጴንጤዎች ሁለት ዓይነት ናቸው፡፡ ሁለቱም የየራሳቸው ክፍፍሎች አሉአቸው፡፡ ሁሉም ግን በልሳን መናገርና በመንፈስቅዱስ መጠመቅ በሚለው ትምህርታቸው ይመሳሰላሉ፡፡ በተቀረውም ሐሳባቸው ግን የፕሮቴስታንት ዘርፎች ናቸው፡፡
- ሁለቱ የጴንጤ ዓይነቶች ዩኒታሪያኒዝምና ትሪኒታሪያን ይባላል፡፡

# 6. ጴንጤዎች (Pentecostalism)

*1. ዩኒታሪያኒዝምና (Unitarianism):-*

- በሥላሴ እናምናለን በማለት ክርስቶስን ከአብና ከመንፈስቅዱስ አሳንሰው የሚመለከቱ ናቸው፡፡

- እንቅስቃሴአቸውንም ኢየሱስ ብቻ *(The Only Jesus Movement)* ብለውታል፡፡

- በአብ በወልድ በመንፈስቅዱስ የተጠመቁ ዳግመኛ በኢየሱስ ስም መጠመቅ ይኖርባቸዋል፤ ካልተጠመቁም አይድኑም በማለት ፀረ-ሥላሴ አቋማቸውን ይገልጣሉ፡፡

- አብ ወልድ መንፈስቅዱስ የማዕረግ እንጂ የአካላት ስሞች አይደሉም፤ አብ ወልድ መንፈስቅዱስ የኢየሱስ የማዕረግ ስሞች ናቸው፤ አብም ወልድም መንፈስቅዱስም ኢየሱስ ብቻ ነው ይላሉ፡፡ የነዚህ ሌላኛው ስማቸው ዋንነስ ቸርች *(Oneness Church)* ይባላል፡፡

- በኢትዮጵያ ያለው ቅርንጫፋቸው የኢትዮጵያ ሐዋርያት ቤ/ክ ተብሎ የሚጠራው ነው፡፡

## 6. ጴንጤዎች (Pentecostalism)

### 2. ትሪኒታሪያን (Trinitarian):-

- ክርስቶስ በማኅፀነ ዮርዳኖስ ጸጋ መንፈስቅዱስን ባይሞላ ኖሮ ሰይጣንን በገዳም (በምድረ በዳ) ሳለ ሊያሸንፈው ወይም ከዚያም በኋላ ተአምራትን ሊሠራ ባልቻለም ነበር በማለት በአማላጅነት መድበውት ፀጋ ሰጪ ሳይሆን ፀጋ ተቀባይ ነው በማለት የክህደት ትምህርታቸውን ያሰራጫሉ::

- እነዚህ ብዙ ቅርንጫፎች አሉአቸው:: ከቅርንጫፎቹም መካከል በ1906 ዓ.ም. የተመሰረተው ሙሉ ወንጌል አማኞች *(Full Gospel)* ተብሎ የተሰየመው ነው::

- እነዚህ በጥቂቱ ሃያ ስድስት ቅርንጫፎች አሉአቸው:: ጥቂቶቹም:- አሴምብሊስ ኦፍ ጎድ (Assemblies of God)፣ ቸርች ኦፍ ጎድ ኢን ክራይስት፣ (Church of God in Christ)፣ ዩናይትድ ፔንቴኮስታል ቸርች (United Pentecostal Church) ተብለው ተሰይመዋል::

- በኢትዮጵያ እነ ሙሉ ወንጌሎች፣ መሰረተ ክርስቶሶች፣ ቤቴልና የመሳሰሉት የዚህ ቅርንጫፎች ናቸው::

አሁንም #*እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን፦ አንሄድባትም አሉ::*; ኤር. 6፡16::

## 7. ሞርሞኒዝም (Mormonism)

- የኋለኛው ቀን (ዘመን) ቅዱሳን የሚባሉት ሲሆኑ በ1825 ዓ.ም. በአሜሪካ ተፈጠሩ። አሁን ወደ 2.5 ሚሊዮን የሚጠጉ ተከታዮች አሉአቸው። መሥራቹ ዮሴፍ ስሚዝ ይባላል።

- ዮሴፍ ስሚዝ #Book of Mormons; የሚል መጽሐፍ ጻፈ። ተከታዮቹም እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ቆጥረው ተቀበሉት። በመጽሐፉ ከክ.ል.በፊት 600 ዓመት አካባቢ ወደ አሜሪካ የተሰደዱ አይሁድ እንደነበሩና እነዚህም በጫካው ለሚኖሩ ሕንዶች መገኛዎች እንደሆኑ፤ እነርሱም በኢየሱስ እንደተጎበኙ፤ ጥበበኞችና ለሕንጻ ሥራም መነሻና ከተሞችንም መገንባት የጀመሩ እነሱ እንደሆኑ ተጠቅሷል።

- ኢየሱስም በጎበኛቸው ጊዜ ያስተማረው ትምህርት በነቢያችን በሞርሞን አማካይነት በወርቅ ጽላት ላይ ተጽፏል ይላሉ።

- ተከታዮቻቸው ቡና ወይም ትምባሆ አይጠቀሙም። አልኮልም አይጠጡም። ብዙ ማግባትም አይከለከሉም። የስሚዝን መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል ነው ብለው ይቀበሉታል። ስሚዝንም እንደ ሙሴ ቅዱስ ነው እንዲያውም ኢየሱስንም ይተካከለዋል ይላሉ።

## 8. ክርስቲያን ሳይንስ (Christian Science

- #Science and Health with Key to The Scripture; የሚባለው መጽሐፍ ለነዚህ እንደ
  ወንጌል ነው፡፡ መጽሐፉም በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መብቂያ ላይ በአሜሪካን አገር በሜሪ ቤከር ኤዲ ተጻፈ፡፡

- ኤዲ እግዚአብሔርን የምትክድ ሲሆን የካልቪንንም ትምህርት ትቃወማለች፡፡ ትምህርታቸውም ከወንጌልም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ፈጽሞ አይገናኝም፡፡

- በመሰብሰቢያቸው ስብከትም ሆነ ሰባኪ የላቸውም፡፡ እስካሁንም ክርስቲያን ሳይንስ ከሌሎች በተለየ መልኩ አልተሰበከም፡፡ ነገር ግን የተመረጡ ሁለት አንባቢዎች ከ"*Science and health*" የተመረጠውን ያነባሉ፡፡ ጥያቄ መጠየቅም ሆነ አስተያየት መስጠት መወያየትም አይፈቀድም፡፡ ሜሬ ቤከር ኤዲ ለክርስቲያን ሳይንስ የመጀመሪያና የመጨረሻ ቃል ናት፡፡ በነዚህ ዘንድ ስለክርስትና በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰበከው ሁሉ ሐሰት ነው ይሉታል፡፡

- በሕክምና ዘዴ አይጠቀሙም፡፡ በነርሱ ዘንድ በሽታ አታላይ ስሜት ስለሆነ ራሳችን ራሳችንን ማከም አለብን ይላሉ፡፡ ሕመምንም ሆነ ኃጢአትን ቦታ አይሰጡትም - ከሁለቱም ለመዳን በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው ሐሰት ነው ይላሉ፡፡

## 8. ክርስቲያን ሳይንስ (Christian Science)…

### 1. ሳይንቶሎጂ (Scientology)

- የዚህ እንቅስቃሴ መሥራቹ ከ1911-1986 ዓ.ም. የኖረው አሜሪካዊው ሮን ሁባርድ ነው፡፡
- ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአልስተር ክሮሌይ ይመራ በነበረው የሰይጣን አምልኮት እንቅስቃሴ ታላቅ ተዋናይ ሆኖ ነበር፡፡
- ሁባርድ በሕይወቱም የመጨረሻ ደቂቃዎች የተደበቀውን ምስጢር #በምድር የነበረው ሥራ እንደነበረውና ሥራውም የክርስቶስን ዳግም መምጣት ለማስቀረት ኢየሱስ ክርስቶስን መቃወም ነበር; በማለት ተናግሮ ሞቷል፡፡
- የራሱን ሃይማኖት መፍጠሩም ባለጠጋና ትርፋማ አድርጎት ነበር፡፡ ሲሞትም 640 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ሀብት ነበረው፡፡
- በአሁኑ ወቅት ዳቪድ ሚስከቪጅ በሚባል መሪ የሚመሩ ሲሆኑ ዋና ማዕከላቸውም በሎስ አንጀለስ፤ መንፈሳዊ አስተዳደሩም በፍሎሪዳ፤ ለአውሮፓ ዋና ማዕከላቸውን በኮፐንሀገን አድርገው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡
- የሥነ ልቦና ምርምር፤ የምትሐት፤ የክህደትና የሳይንሳዊ ልብወለድ ቅልቅል ነው፡፡
- ራሳቸውን እንደ ሃይማኖታዊ ተቋም በመቁጠር #ቤተ ክርስቲያን; ነን ይላሉ፡፡ ነገር ግን ሁባርድ ራሱ በተናገረው ቃል #ገንዘብህን ስጥ - ብዙ ገንዘብም ይኑርህ - ሰዎች ሁሉ እንዲሠሩ አስገድዳቸው - በዚህም የተነሳ ብዙ ገንዘብ ይኖራቸዋል፡፡; በማለት እንደገለጸው ዋና ዓላማቸው ንግድ ነው፡፡
- ሁባርድ ከመሞቱ አስቀድሞ ዳግም ፓለቲከኛ ሆኖ እንደሚመጣ ተናግሮ ነበር፡፡

# ሴንቶሎጂ...

- ከስህተት፤ ወንጀል፤ ጦርነት፤ አደንዛዥ ዕፅ የጸዳች ዓለም እንፈጥራለን ይኽም አስቀድሞ በሁሉም ደረጃ ከመንግሥት ጀምሮ መተግበር አለበት የሚል ተልእኮ አላቸው፡፡ ፡፡

- ዓላማቸውንም ለማሳካት ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን ምሁራን በሁባርድ ኮሌጅ በሚሰጡት የAdministrative Technology ትምህርት አማካይነት ይቀጥራሉ፡፡ ዓላማቸውም እስካሁን ያለውን አስተሳሰብ አጥፍቶ የሴንቶሎጂ አስተሳሰብ መቅረጽ ነው፡፡

-

- የመጨረሻ ግባቸውም እንደ ሴንቶሎጂ ሕግ የሚራመድ አዲስ ሰውና አዲስ ዓለም መፍጠር ነው፡፡ በዚህም የሚመራ ኅብረተሰብ ነጻነቱንና መብቱንም ስለሚነጠቅ ይህ መሆኑ ለዓለማችን ሞት ይሆናል፡፡ የነዚህ ቡድኖች ቅርንጫፎች ያሉአቸው አገሮች ሁሉ የሴንቶሎጂን እንቅስቃሴ በመከታተልና በመመርመር ሥራ የተጠመዱ ናቸው፡፡

- በዚህ ሥር ከሚካተቱት ሌላው Secular Humanism ነው፡፡ ይህም ክርስቲያናዊ ተቋማትን ለትምህርት፤ ለሰው ኑሮና ሥነ ልቦና እንቅፋት አድርጎ ይቆጥራቸዋል፡፡ ሰውም ከሁሉም በላይ ስለሆነ ሕግን ለማውጣትም ሆነ ለመኖር የእግዚአብሔር እገዛ አያስፈልገውም ይላሉ፡፡

- ቤተክርቲያን የሌለችበት ክርስትናም ሌላው የማይረሳ የዘመናችን የክህደት እንቅቃሴ ነው፡፡

*እግዚአብሔር በኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታችን አጽንቶ ይጠብቀን፡፡*

ይቀጥላል...

ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶችና የዮዋ ምስክሮች
(Jehovah Witness)
...

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።